# የ 2023-2025 መመሪያዎች

Waste-Free Communities Matching Grant
(ከብክለት ነፃ የሆኑ ማህበረሰቦች የማቺንግ ድጎማ)

Seattle Public Utilities








## የማመልከቻዎች የመጨረሻ ግዜ ማርች 24፣ 2023 5:00 pm ላይ ነው

Seattle Public Utilities (SPU፣ የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች) አሁን በቆሻሻ ላይ ላተኮሩ የማህበረሰብ ፕሮጄክቶች የማቺንግ ድጋፎችን ለመስጠት ማመልከቻዎችን እየተቀበለ ነው። ቆሻሻን መከላከል ማለት አነስተኛ ቁሳቁሶች መልሰው ጥቅም እንዲሰጡ፣ ማዳበሪያ፣ እና ቆሻሻ መጣያ ውስጥ እንዲገቡ ለማድረግ አነስተኛ ብክነትን መፍጠር ማለት ነው። ብክነትን በምንከላከልበት ጊዜ፣ አካባቢን እንረዳለን፣ የህብረተሰብ ጤናን እንጠብቃለን፣ ማህበረሰብን እንገነባለን፣ እንዲሁም ገንዘብ እንቆጥባለን።

### የድጎማ ፕሮግራም ዓላማዎች፦

- በቆሻሻ መከላከል ዙሪያ የህብረተሰቡን አመራር እና ፈጠራን ይደግፉ
- የቆሻሻ መከላከል እድሎች እና ጥቅሞች ላይ የህብረተሰቡን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ
- የተፈጥሮ ሀብትን በመጠበቅ እና የግሪንሀውስ ጋዝ ልቀቶችን እና ሌሎች በካዮችን በመቀነስ አካባቢን እና የህዝብ ጤናን መጠበቅ
- በሲያትል ውስጥ የሚባክኑትን የቁሳቁሶች መጠን ይቀንሱ

### የእርዳታ ኣጠቃላይ እይታ

- ይህንን የእርዳታ ዑደት ለመሸለም አጠቃላይ $200,000 አለ።
- የስጦታ ጥያቄዎች ከ $3,000 እስከ $40,000 ሊደርሱ ይችላሉ። SPU ከተጠየቀዉ መጠን በታች ወይም በላይ ሊረዳ ይችላል።
- 25% የማች መስፈርት አለ። ምሳሌ፦ $40,000 የገንዘብ ድጋፍ + $10,000 ማች = $50,000 ጠቅላላ የፕሮጀክት በጀት።
- የስጦታ ሽልማቶች ገንዘብን በማወራረድ/ወጪን በማካካስ መሠረት ይከፈላሉ። ሽልማት ወሳጆች የፕሮጀክት ማስጀመሪያ ወጪዎችን ለመደገፍ ከጠቅላላ የስጦታ ሽልማት እስከ 10% በቅድሚያ ሊጠይቁ ይችላሉ።
- ፕሮጀክቶች ከጁላይ 2023 በፊት ሊጀምሩ ይችላሉ። ገንዘብ ከጁን 30፣ 2025 ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል እና ደረሰኝ መግባት አለበት።

## ስለ ቆሻሻ መከላከል

ሪሳይክል ማድረግ እና ማዳበሪያ መስራት በጣም ጥሩ ናቸው። በመጀመሪያ ደረጃ ቆሻሻ አለመፍጠር ግን የበለጠ የተሻለ ነው!

የምንገዛው ወይም የምንጠቀመዉ ማንኛዉም ነገር ምርቱን እና ማሸግያዉን ለመስራት፣ ለማጓጓዝ፣ ለመጠቀም እንዲሁም መልሶ ለመጠቀም፣ ማዳበሪያ ለማድረግ ወይም መሬት ዉስጥ እንዲበሰብስ ለማድረግ ሀብትን ይጠይቃል። ይህ ሁሉ በምንተነፍሰው አየር፣ በምንጠጣው ውሃ እና ምግብ በምናበቅልበት አፈር ላይ ትልቅ ተጽህኖ አለው።

### በሚከተሉት ብክነትን መከላከል እንችላለን፦

- ያነሰ በመግዛት እና በመጠቀም
- ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆዩ ምርቶችን በመስራት ወይም በመግዛት
- አነስተኛ ማሸጊያዎችን በመጠቀም
- መጠገንን፣ መልሶ መጠቀምን እና ጥቅም ላይ የነበረዉን ድጋሚ መጠቀምን መምረጥ
- ሌሎች እንደገና እንዲጠቀሙባቸው እቃዎችን ማጋራት፣ መለገስ ወይም እንደገና መሸጥ
- በቦታው ላይ የምግብ እና የጓሮ ቆሻሻን በማዘጋጀት እና በመጠቀም

### ብክነትን ለመከላከል እርምጃ በመውሰድ፣ እኛ፦

- ያነሰ በመግዛት እና በመጠቀም ገንዘብ እንቆጥባለን
- በመለገስ እና በማካፈል ማሕብረሰባችንን መርዳት
- የሰውን ጤንነት እና የዱር እንስሳትን የሚጎዳ የአየር እና የውሃ ብክለትን እንቀንሳለን
- እንደ ውሃ፣ ኃይል፣ መሬት እና ነዳጅ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን እንቆጥባለን
- የአየር ንብረት ለውጥን የሚያስከትሉ የግሪንሃውስ ጋዝ ልቀቶችን እንቀንሳለን

**ጥያቄ? Veronica Fincher ን በ WasteFreeGrants@seattle.gov ወይም በ (206) 615-1405 ያግኙ።**
www.seattle.gov/utilities/wastefreegrants

## የፕሮጀክቱ መስፈርቶች

ፕሮጀክቶች ብቁ ለመሆን የሚከተሉትን መስፈርቶች ሁሉ ማሟላት ኣለባቸዉ።

1. **እንቅስቃሴዎች <u>ቆሻሻ መከላከልን መጨመር</u> አለባቸው።**

   የብቁ ፕሮጀክቶች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

   - ረዳት የሚፈልጉ ሰዎች ባሉባቸዉ የመኖሪያ ተቋማት ድጋሚ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል የምግብ ቦርሳ መርሃ ግብር መሞከር
   - በምግብ ለጋሾች እና የረሃብ እርዳታ ድርጅቶች መካከል ያለውን ተግባቦት ለማሻሻል የሙከራ ስልቶች
   - መልሶ ጥቅም የሚዉሉ የመሸከፊያ መያዣዎች ስርዓት መዘርጋት
   - የኪራይ እቃዎች መጋዘኖች መክፈት ወይም ማስፋፋት
   - የተማሪዎችመኖሪያ ላይ ባሉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የምግብ ብክነት ለመከላከልየሙከራ ስልቶች
   - ብክነትን ለመከላከል የሚጠቅሙ ያሉዎት ሌሎችየፈጠራ ሀሳቦች!

   የሚከተሉት ተግባራት ለእርዳታ ገንዘብ ብቁ አይደሉም፦

   - አሁን ባሉበት ብክነት የመከላከል ደረጃ እንቅስቃሴዎችን ለማስቀጠል ቀጣይ የስራ ማስኬጃ ወጪዎች
   - ሪሳይክል ማድረግ
   - ከቦታ ውጭ ማዳበሪያ (ሌላ ቦታ የተዘጋጀ እና ጥቅም ላይ የዋለ)
   - ሪሳይክል ወይም ማዳበሪያ የሚደረጉ ምርቶችን መጠቀም
   - ቆሻሻን የማጽዳት ተግባራት
   - የቢስክሌት እና የመኪና ድርሻዎች

2. **እንቅስቃሴዎች በ <u>የሲያትል ከተማ ወሰን</u> ውስጥ መከናወን አለባቸው ወይም በሲያትል ውስጥ በቆሻሻ ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ማሳደር አለባቸው።**

   ፕሮጀክቱ ከሲያትል የቆሻሻ ፍሰት ጋር ያለውን ጠንካራ ግንኙነት በግልፅ እስካሳየ ድረስ አመልካቾች ከሲያትል ውጭ ሊሆኑ ይችላሉ።

   የሲያትል ከተማ ወሰን ካርታ ይመልከቱ፦ http://clerk.ci.seattle.wa.us/~public/nmaps/fullcity.htm

3. **እንቅስቃሴዎች ከሚከተሉት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች <u>አንዱን ወይም ከዚያ በላይ</u> ማሳደግ አለባቸዉ፦**

   **A) ፈጠራ፦** ኣዳዲስ ዘዴዎች ወይም ቴክኖሎጂ መሞከር ወይም ማስፋፋት ወይም ኣዳዲስ ቆሻሻ መከላከያ ዕድሎችን ወደ ሲያትል ማስመጣት።

   <u>የቀደምት/ያለፉ ፕሮጀክቶች ምሳሌዎች፦</u>

   - ነጻ ተንቀሳቃሽ የማሕበረሰብ መደብር መሞከር
   - ለአዳዲስ ግንባታ የተመለሰውን ጣውላ ለመጠቀም የንግድ ስራን ማሳየት

   **B) ፍትሃዊ ተደራሽነትን እና ተሳትፎን ማስፋፋት፦** ብክነት የመከላከል ተግባራት ላይ በታሪክ እና በአሁኑ ጊዜ ከተገለሉ ማህበረሰቦች ጋር በብቃት መሳተፍ። ቅድሚያ የሚሰጣቸው ማህበረሰቦች ምሳሌዎች የአገሩ ተወላጆች፣ አፍሪካ አሜሪካውያን፣ ስደተኞች፣ ጥገኞኞች፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው፣ አካል ጉዳተኞች፣ LGBTQIA2+፣ አዛውንቶች፣ ጎልማሶች፣ ወጣቶች፣ ልጆች እና/ወይም ትናንሽ ንግዶች።

   <u>የቀደምት/ያለፉ ፕሮጀክቶች ምሳሌዎች፦</u>

   - በማህበረሰብ ጥገና ኹነቶች ላይ ለመሳተፍ አዛውንቶችን መመልመል
   - አነስተኛ ንግዶች ብክነትን ለመከላከል የሚረዱ ግብዓቶችን ማቅረብ

   **C) ፍትሀዊ የማህበረሰብ ጥቅማ ጥቅሞችን ማሳደግ፦** በታሪክ እና ኣሁን ላይ ለተገለሉ ማሕበረሰቦች የብክነት መከላከል ጥቅሞችን መጨመር፦ ለምሳሌ ቤት ለሌላቸዉ ወይም የምግብ ችግር ላለባቸዉ ሰዎች ነጻ ወይም በኣነስተኛ ዋጋ ግብዐቶች ወይም የስራ ስልጠና ዕድሎችን መጨመር።

   <u>የቀደምት/ያለፉ ፕሮጀክቶች ምሳሌዎች፦</u>

   - ኢሚግራንት እና ስደተኛ ሴቶችን ከባከነ ጨርቃጨርቅ የተሠሩ የቤት እቃዎችን እንዲፈጥሩ እናእንዲሸጡ መቅጠር
   - ከአፓርታማ ተከራዮች ለቀው ሲወጡ የማይበሰብስ ምግብ ሰብስበው ለአከባቢው የምግብ ባንኮች መለገስ

ከላይ ከተዘረዘሩት መስፈርቶች በተጨማሪ ዋና ተወዳዳሪ የሆኑ ማመልከቻዎች የሚከተሉት ይኖሩዋቸዋል፡-

- የእርዳታ ፕሮጀክቱ መፍታት የሚችለዉ በግልጽ የተቀመጠ ፈተና ወይ ጥያቄ
- በእርዳታ ፕሮጀክቱ ወቅት ወይም በኋላ ማንኛውንም የጥናት ምክሮች ወይም መሳሪያዎች ለመጠቀም የሚያስችል እቅድ
- እርዳታዉ ከተጠናቀቀ በኋላ ፕሮጀክቱን ለማስቀጠል፣ ለማስፋፋት ወይም ቀጣይ ደረጃዎች ላይ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ እቅድ
- ከአንድ ድርጅት ወይም ንግድ በላይ የሆነ ተጽእኖ ማሳደር። ለምሳሌ፡- የእርዳታ ፕሮጀክቱን ተደራሽነት ለማስፋፋት ከሌሎች ጋር በመሻረክ፣ ፕሮጀክቱ ላይ ማሕበረሰቡን ማሳተፍ ወይም ሌሎች በሲያትል ውስጥ ተመሳሳይ የቆሻሻ መከላከል ጥረቶችን እንዲተገብሩ ለመርዳት በፕሮጀክቱ የተገኘውን እውቀት ማካፈል።

## ማመልከት ያለበት ማነው

SPU ማመልከቻዎችን ከሚከተሉት ያበረታታል፡-

- ከንግዶች
- ለትርፍ ካልተቋቋሙ ድርጅቶች
- ከማህበረሰብ እና ከሰፈር ቡድኖች
- ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆች፣ እና ዩኒቨርስቲዎች
- ተቋማት (እንደ ጤና አጠባበቅ ወይም መኖሪያ ቤት ያሉ)
- በእምነት ላይ የተመሰረቱ ድርጅቶች
- የወጣቶች እና የልጆች ፕሮግራሞች

አመልካቾች ከኣንድ በላይ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ ነገር ግን በየ ኣንድ የእርዳታ ዙር ኣንድ መቀበል የሚችሉት እርዳታ ኣንድ ብቻ ነዉ።

ሁሉም አመልካቾች የገንዘብ ድጎማዎችን ለመቀበል፣ ወይም አስፈላጊ በሆኑ ፈቃዶች በፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪል በኩል ለመስራት የዋሺንግተን ግዛት እና የሲያትል ከተማ የንግድ ፈቃዶች ሊኖራቸው ይገባል። የገንዘብ ወኪል ለአንድ ፕሮጀክት የድጋፍ ገንዘብ ለመቀበል እና ለማስተዳደር ኃላፊነቱን ይወስዳል።

**የሲያትል ከተማ የንግድ ስራ ፈቃድ መረጃ፡-** https://www.seattle.gov/office-of-economic-development/small-business/food-businesses/licensing።
**የዋሺንግተን ግዛት የንግድ ስራ ፈቃድ መረጃ፡-** https://dor.wa.gov/

### እንደገና ማመልከት

አመልካቾች ለእያንዳንዱ የገንዘብ ድጋፍ ዑደት እንደገና ማመልከት ይችላሉ፡-

- የገንዘብ ድጋፍ ባልተሰጠው ፕሮጀክት እንደገና ማመልከት ለሚቀጥለው የገንዘብ ድጋፍ ዑደት እንዴት ማመልከቻዎን ማሻሻል እንደሚችሉ ለማወቅ እንዲያነጋግሩን እንመክራለን።
- በአዲስ የፕሮጀክት ሀሳብ ማመልከት።
- ቀደም ሲል በገንዘብ የተደገፈ ፕሮጀክት ለማስፋት ወይም ቀጣዩን ምዕራፍ ለመተግበር ማመልከት። ማመልከቻው የተሻሻለ የቆሻሻ መከላከልን ማሳየት አለበት። የእርዳታ ገንዘቦች አሁን ባለው የቆሻሻ መከላከል ደረጃ ፕሮጀክትን ለማስቀጠል ጥቅም ላይ ላይዉሉ ይችላሉ።

## የገንዘብ ድጋፍ እና የማች መስፈርቶች

### የገንዘብ ድጋፍ፡-

- ይህንን የእርዳታ ዑደት ለመሸለም አጠቃላይ $200,000 አለ።
- የስጦታ ጥያቄዎች ከ $3,000 እስከ $40,000 ሊደርሱ ይችላሉ። SPU ከተጠየቀዉ መጠን በታች ወይም በላይ ሊረዳ ይችላል።
- የእርዳታ ገንዘቦች ከጁን 30፣ 2025 ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል እና ደረሰኝ መግባት አለበት።

### የሚፈቀዱ ወጪዎች

የሚከተሉት ለድጎማ የገንዘብ ድጋፍ ብቁ ሊሆኑ የሚችሉ የወጪዎች ምሳሌ ናቸዉ፡-

- ለእርዳታ ፕሮጀክቱ የተመደበው የሰራተኞች ጊዜ (ተዘዋዋሪ ወጪዎችን ሊያካትት ይችላል)
- ለፕሮጀክት ተሳትፎ ኣበሎች እና ሌሎች ማበረታቻዎች
- የፕሮጀክት አቅርቦቶች፣ እቃዎች እና መሳሪያዎች
- እንደ ትርጉም፣ ህትመት፣ እና ዲዛይን ያሉ አገልግሎቶች

- ለፕሮጀክት ስራዎች የቦታ ኪራይ
- የአልኮል መጠጦችን ሳይጨምር፣ ለፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ምግብ እና መጠጥ
- ለፕሮጀክት ስራዎች የጉዞ እና የመኪና ማቆሚያ (በፌዴራል የጉዞ ርቀት መጠን ዋጋ የሚወጣለት)
- የፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪል ክፍያዎች (የእርዳታን ጥያቄ እስከ 10%)

### የማች መስፈርቶች

አመልካቾች በድጎማ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን ወጪዎች መካፈል አለባቸው።

- መጠኑ ከተጠየቀዉ ድጎማ ቢያንስ 25% መሆን አለበት።
  ምሳሌ፦ $40,000 የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄ + $10,000 ማች = $50,000 ጠቅላላ የፕሮጀክት በጀት።
- የጡረታ መዋጮዎች ለድጎማዉ ፕሮጀክት የተወሰነ መሆን አለባቸው። ይህ የፕሮጀክቱን የተወሰነ ክፍል ለመደገፍ የሚያገለግል የጥሬ ገንዘብ ወይም ሌላ የእርዳታ ገንዘቦች እና የእርዳታ ፕሮጀክቶችን የሚደግፉ እንደ የበጎ ፈቃደኞች ሰዓት፣ ቦታ፣ አገልግሎቶች እና አቅርቦቶች ያሉ እርዳታዎችን ሊያካትት ይችላል።
- የዋሽንግተን ግዛት የገለልተኛ ሴክተር የበጎ ፈቃደኝነት ሰዓት ዋጋ ላይ በመመስረት የማይከፈልዉ የበጎ ፈቃድ ሰዓታት$34.87 በሰአት ይገመታል።
- እንደ ከተማ ሰራተኛ ሰዓት፣ የከተማ መገልገያዎችን አጠቃቀም፣ እና/ ወይም ሌላ የከተማ ገንዘብን የመሳሰሉ የሲያትል ከተማ ሀብቶች እንደ ማች አካል አይቆጠሩም።

## ውል እና ክፍያ

### የፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪሎች፦

አመልካቾች ለፕሮጀክቱ የእርዳታ ገንዘብን ለመቀበል እና ለማስተዳደር ኃላፊነቱን ከሚወስድ የፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪል ጋር ለመስራት ይመርጡ ይሆናል። አመልካቾች የራሳቸውን የፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪል በመለየት እና የፊስካል ወኪሉ የወቅቱ የዋሽንግተን ግዛት እና የሲያትል የንግድ ፍቃዶች እንዳላቸው የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው። የፊስካል/የገንዘብ አያያዝ ወኪል ክፍያዎች የእርዳታውን መጠን እስከ 10% ያህል ሊያከፍሉ ይችላሉ። አመልካቾች ይህንን ክፍያ በእርዳታ ጥያቄው ውስጥ ሊያካትቱ ወይም በማች መዋጮ ላይ ማመልከት ይችላሉ።

### ውል፦

እያንዳንዱ ድጋፍ ተቀባይ ወይም የገንዘብ ወኪላቸው የ W9 ቅጽ ማቅረብ እና የእርዳታ ገንዘቦችን ለመቀበል ከ SPU ጋር ስምምነት መፈረም አለባቸው። ስምምነቱ የእርዳታውን ተጨማሪ ውሎች እና ሁኔታዎችን ያጠቃልላል።

እርዳታው ከከተማው ጋር ስምምነት ከተፈረመ በኋላ ለሚከናወኑ የፕሮጀክት ተግባራት ብቻ ይከፍላል።

### የመድን መስፈርቶች፦

ድጋፍ ተቀባዮች ወይም የገንዘብ ወኪላቸው በዋሽንግተን ግዛት ሕግ ከሚጠይቀው ያላነሰ ዓላማ እና ስፋት እና ተፈጥሮ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሥራ ለሚያከናውኑ ንግዶች እንደ ዓይነተኛ የመድን ደረጃዎችን መጠበቅ አለባቸው። በዋሽንግተን ግዛት ሕግ የሚጠየቅ ከሆነ የሰራተኞች የካሳ መድን እንዲሁ ሊቆይ ይገባል።

### ክፍያ፦

የስጦታ ሽልማቶች ገንዘብን በማወራረድ/ወጪን በማካካስ መሠረት ይከፈላሉ። እርዳታ ተቀባዮች በእርዳታዉ ስምምነቱ ውስጥ የተገለጹትን ልዩ ክንውኖችን ሲያጠናቅቁ ወይም በትክክለኛ ወጪዎች ላይ ተመስርተው ደረሰኞችን ያቀርባሉ። SPU እያንዳንዱ የክፍያ መጠየቂያ ደረሰኝ ከደረሰ ከ 30 ቀናት በኋላ ተመላሽ ገንዘብ ቼኮችን በፖስታ ይልካል። የክፍያ መጠየቂያዎች ያልተጠናቀቁ ወይም አስፈላጊ ሪፖርቶች እና ሰነዶች ከሌሉ ክፍያው ይዘገያል።

<u>እርዳታ ተቀባዮች የፕሮጀክት ማስጀመሪያ ወጪዎችን ለመደገፍ እስከ 10% የሚሆነውን የገንዘብ ድጋፉን አስቀድመው ሊጠይቁ ይችላሉ።</u> ጥያቄው ኣስቀድሞ የሚለቀቅ ገንዘብ ኣስፈላጊነቱን እና እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል በግልጽ ማብራራት ኣለበት። ገንዘብ ተቀባዩ ለቀሪው የእርዳታ ገንዘብ ክፍያ እንዲሰጠዉ ከመፈቀዱ በፊት የገንዘቡ አጠቃቀም ማረጋገጫ ቀርቦ በ SPU መጽደቅ አለበት። እርዳታ ተቀባዩ በቂ የሆነየማረጋገጫ ሰነድ ካላቀረበ SPU የተወሰነ ወይም ሁሉንም የቅድሚያ ገንዘቦች መመለስ ያስፈልገዋል።

**ሪፖርት ማድረግ፦**

SPU የፕሮጀክት ተግባራትን፣ ውጤቶችን፣ ፈተናዎችን፣ ስኬቶችን እና የተማሩትን ለመሰነድ ዝግጁ የሆነ የሪፖርት ንድፍ ለማዘጋጀት ከእያንዳንዱ እርዳታ ተቀባይ ጋር ይሰራል። የእርዳታ ተቀባዮች ሪፖርቶችን ፕሪንት አድርገው ወይም በቪዲዮ መልክ ለማቅረብ ወይም ከ SPU ሰራተኞች ጋር የቃል ሪፖርቶችን ለማቅረብ መምረጥ ይችላሉ።

ሪፖርቶች ከእያንዳንዱ ደረሰኝ ጋር መቅረብ አለባቸው እና የመጨረሻውን የእርዳታ ክፍያ ከመቀበሉ በፊት የመጨረሻው ሪፖርት መቅረብ አለበት። የመጨረሻውን ሪፖርት ለመገምገም እና ጥያቄዎችን እንዲያብራሩለት ለመጠየቅ SPU ከእያንዳንዱ እርዳታ ተቀባይ ጋር ስብሰባ ሊጠይቅ ይችላል።

## የማመልከቻ ግምገማ

**የግምገማ ኮሚቴ፦**

የእርዳታ ግምገማ ኮሚቴው ከተለያዩ መነሻ እና የሙያ ዘርፎች የተውጣጡ የማህበረሰብ አባላት እና የሲያትል ከተማ ሰራተኞች ናቸው። SPU አመራር የመጨረሻ የገንዘብ ድጋፍ ውሳኔ ሲያደርግ የግምገማ ኮሚቴ ምክሮችን ከግምት ውስጥ ያስገባል።

**የግምገማ መስፈርት/መመዘኛ፦**

የእርዳታ ግምገማ ኮሚቴው ከዚህ በታች በተገለፁት መመዘኛዎች መሠረት ለፕሮጀክቶች ቅድሚያ ይሰጣል። SPU እንዲሁም በጂኦግራፊያዊ አካባቢ፣ ተጽዕኖ በደረሰባቸው ማህበረሰቦች እና የፕሮጀክቶች ዓይነቶች ብዝሃነትን ይመለከታል። SPU የመጨረሻውን የገንዘብ ውሳኔ ከማድረጉ በፊት አመልካቾችን በክትትል ጥያቄዎች አማካይነት ሊያነጋግራቸው ይችላል።

1. **ቆሻሻን የመከላከል ውጤቶች፦** የፕሮጀክት ቆሻሻን የመከላከል አቅም።
    - ፕሮጀክቱ ለ SPU በጣም ቅድሚያ የሚሰጣቸዉን ቁሳቁስ ብክነትን ይከላከላል (የአሁን ቅድሚያ የሚሰጣቸዉ፦ ምግብ፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ ለአንድ ነገር ብቻ የሚጠቅሙ ነገሮች፣ የግንባታ መሳርያዎች፣የቤት እቃዎች እና ቁሳቁሶች)
    - እርዳታ በሚደረግለት ፕሮጀክቱ ወቅት እና ለወደፊቱ እና ተዛማጅ የአካባቢ እና የጤና ተጽእኖዎች ላይ የፕሮጀክቱ ቆሻሻ የመከላከል አቅም
    - ፕሮጀክቱ ውጤታማ በሆነ መንገድ ሊደርስ የሚችለዉ የሰዎች ብዛት
    - ፕሮጀክቱ በሲያትል ውስጥ የቆሻሻ መከላከያ ግብዐቶችን ለማስፋፋት እና/ወይም ለሌሎች ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ቁልፍ ፈተና ለመፍታት ወይም አዲስ እውቀት ለማግኘት ይፈልጋል

2. **የፕሮጀክት አቅም፦** የፕሮጀክት የመሳካት አቅም አቅምን መሰረትያደረገ ነው።
    - ፕሮጀክቱ ስኬታማ ለመሆን በቂ ሰራተኞች፣ አጋሮች፣ በጎ ፈቃደኞች እና የገንዘብ ምንጮች አሉት
    - የፕሮጀክቱ ሰራተኞች፣ በጎ ፈቃደኞች እና አጋሮች የሚፈለገዉን እውቀት፣ ችሎታ፣ ልምድ እና ግንኙነት አላቸው።
    - አስፈላጊ ከሆነ አጋርነቶች ቀድመው የተረጋገጡ ናቸው

3. **የፕሮጀክት በጀት፦** በታቀደው በጀት መሰረት የፕሮጀክት ስኬት የመሳካት አቅም
    - በጀት ከፕሮጀክት ፕሮፖዛል ጋር የሚስማማ ነው
    - የበጀት ግምቶች ትክክል ናቸው
    - ወጪዎች ለእርዳታዉ ተስማሚ ናቸው
    - ለተጠበቀው ውጤት የተጠየቀው መጠን ተመጣጣኝ ነው

4. **ቅድሚያ የሚሰጣቸው፦** ፕሮጀክቶች ከሚከተሉት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ማራመድ አለባቸው።

    **A) ፈጠራ፦** የአንድ ፕሮጀክት አዲስ አቀራረቦችን ወይም ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም።
    - ፕሮጀክቱ ለሲያትል አካባቢ ፈጠራን ያማከለ ነው
    - ፕሮጀክቱ በሲያትል ውስጥ ትልቅ ተፅዕኖ ለመፍጠር የመስፋፋት አቅም አለው።
    - ፕሮጀክቱ ሌሎች በሲያትል ውስጥ ተመሳሳይ የቆሻሻ መከላከል ጥረቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ መሳሪያዎችን እና ግብዐቶችን እና የተገኘውን እውቀት ያካፍላል

B) **ፍትሃዊ ተደራሽነትን እና ተሳትፎን ማስፋፋት፡-** በታሪክ እና በአሁኑ ጊዜ የተገለሉ ማህበረሰቦችን በቆሻሻ መከላከል ተግባራት ውስጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማሳተፍ የፕሮጀክቱ አቅም።

- ፕሮጀክቱ የአገሬው ተወላጆችን፣ አፍሪካ አሜሪካውያንን፣ ስደተኞችን፣ ጥገኞችን፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ LGBTQIA2+ን፣ አዛውንቶችን፣ ጎልማሶችን፣ ወጣቶችን፣ ልጆችን፣ ትናንሽ ንግዶችን እና/ወይም ሌሎች ያልተካተቱ ማህበረሰቦችን የሚያሳትፍ ይሆናል።
- ፕሮጀክቱ ለሚሳተፉ እያንዳንዱ ማህበረሰብ ውጤታማ የሚሆኑ ስልቶችን ይጠቀማል
- ፕሮጀክቱ በፕሮጀክት እቅድ እና ትግበራ ላይ ተጽዕኖ ያደረባቸውን ማህበረሰቦችን ያካትታል

C) **ፍትሃዊ የማህበረሰብ ጥቅማ ጥቅሞችን ማሳደግ፡-** በታሪክ እና በአሁኑ ጊዜ ያልተካተቱ ማህበረሰቦች የቆሻሻ መከላከል ጥቅሞችን ለማሳደግየፕሮጀክት ኣቅም።

- ፕሮጀክቱ እንደ ቤት እጦት ያለባቸዉ ወይም የምግብ ዋስትና የሌላቸዉ ያሉ በጣም የተቸገሩ ሰዎች ይጠቅማል
- የተለዩ ጥቅማጥቅሞች ለተጎዱት ማህበረሰቦች ጠቃሚ ይሆናሉ ለምሳሌ፡- ነፃ ወይም ዝቅተኛ ወጪ ሀብቶችን ማቅረብ ወይም የስራ ስልጠና መስጠት

## የማመልከቻ ሂደት

### መርሃ ግብር፡-

| | |
|---|---|
| የማመልከቻ ማብቂያ | ማርች 24/2023 |
| የውሳኔዎች ማስታወቂያ | ሜይ ኣጋማሽ ላይ |
| ስምምነቶች በ ከተማ የተፈረሙ (ፕሮጀክቶች ሊጀምሩ ይችላሉ) | ጁላይ 2023 |
| ስራ ተጠናቅቋል እና መጠየቂያ ደረሰኝ ገብቷል | በጁን 30፣ 2025 |

### የማመልከቻ ደረጃዎች፡-

**ደረጃ 1፡-** ማመልከቻዎን ከማጠናቀቅዎ በፊት መመሪያዎቹን ያንብቡ እና የእርዳታ ትእዛዞች ቪዲዮን ይመልከቱ።

**ደረጃ 2፡-** ፕሮጀክትዎን ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ እና የፕሮጀክት ምክሮችን ለማግኘት ያግኙን። WasteFreeGrants@seattle.gov ወይም (206) 615-1405

**ደረጃ 3፡-** የህትመት ወይም ቪዲዮ ማመልከቻን ያጠናቅቁ (ሁለቱንም አያድርጉ)።

- የህትመት ማመልከቻዎች ከ 10 ገጾች ያልበለጡ መሆን አለባቸው።
- የቪዲዮ ማመልከቻዎች ከ 15 ደቂቃዎች ያልበለጡ መሆን አለባቸው።
- ማመልከቻዎች በሚመርጡት ቋንቋ ሊቀርቡ ይችላሉ። Seattle Public Utilities (SPU፣ የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች) ትርጉም ይሰጣል።

**ደረጃ 4፡-** የእርዳታ ማመልከቻዎን እና ደጋፊ ሰነዶችን በማርች 24/2023 ከቀኑ 5፡00 ሰዓት ድረስ ያስገቡ። በ 2 የስራ ቀናት ውስጥ የደርሰናል ኢ-ሜይል ማረጋገጫ ካልደረሰዎት በ (206) 615-1405 ይደውሉ።

## የቋንቋ እርዳታ

በሚቀጥሉት ቋንቋዎች እገዛ ለማግኘት አጋራችንን፣ Environmental Coalition of South Seattle (ECOSS፣ የደቡብ ሲያትል አካባቢያዊ ጥምረት) በ emak@ecoss.org ወይም በ (206) 767-0432 ያነጋግሩ።

ለእርዳታ አመልካቾች የቋንቋ እርዳታ ለመስጠት SPU ለECOSS የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል።

- አማርኛ
- ካንቲኒዝ
- ማንዳሪን
- ስፓኒሽ
- ትግርኛ
- ቪዬትናምኛ